# ጅማ አባ ጅፋር የእግር ኳስ ክለብ የዲሲፕሊን ውሳኔን ተግባራዊ ባለማድረጉ ከየካቲት 29/2011 ጀምሮ ፌዴሬሽኑ ከሚያዘጋጃቸው ውድድሮች መታገዱ ተገለፀ፡፡

ወጣት አብዱልፈታ ከማል የክለቡ እግር ኳስ ቡድን ተጨዋች ከክለቡ ጋር ውል እያለው ከመስከረም ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ውሉ በክለቡ በመቋረጡ ባቀረበው አቤቱታ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ተመልክቶ ለአመልካች ያልተከፈለው ደመወዝ ታስቦ በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ክለቡ እንዲከፍል በ12/06/2010 በተጻፈ ደብዳቤ ዲሲፕሊን ኮሚቴው ያሳወቀ ቢሆንም ተግባራዊ ሳይደረግ በመቆየቱ በ12/08/2010 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቀጣይ እርምጃ ክለቡ ላይ እንደሚወስድ ያሳወቀ ቢሆንም ይህንን ውሳኔ ተግባራዊ ሣያደርግ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ከየካቲት 29/2011 ዓ.ም ጀምሮ ክለቡ ፌዴሬሽኑ ከሚያዘጋጀው እግር ኳስ ውድድር የታገደ መሆኑን የዲሲፕሊን ኮሚቴው አሳውቆናል፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት